ተልዕኮአችን

ሐምሌ 2012 | ቅጽ 4



ተልዕኮአችን

በውስጥ ገጾች

የመጽሐፍ ትርጉም ለምን አስፈለገ? / ONE SOUL SAVED MATTER /
መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ / የጽናት ተምሳሌቷ ሜርሊን ሎስዛሎ / መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰሜን ኮሪያ እንዴት ገባ / የጸሎት ጥሪ ለስልጤ የህዝብ ክፍል / ዋይክሌፍ የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተቋም እና ስራዎቹ /
የክርስቲያኖች ስደት በሶማሊያ

መልዕክት

ተልዕኮአችን ዲጂታል መጽሔይት አማኞችን በወንጌል ዙሪያ ለማስተማር እና ለማገዝ የተጀመረ ነው ። ይህ ዲጂታል መጽሔይት ወንጌል እና ተልዕኮ ተኮር ጽሁፎችን፣ ትምህርቶችን እና መልዕክቶችን የምናስተላልፍበት እንደሆነ ባለፉት ሶስት ቅጾች ባወጣናቸው ጽሑፎች አሳይተናል። ያለፉት ሶስት ዕትሞች ብዙዎች ጋር መድረስ የቻለ እና ብዙዎች የተጠቀሙበት እንደሆነ በሚደርሱን መልዕክቶች ለማየት ችለናል ለዚህም ምስጋናችን የላቀ ነው።

ከኢንተርኔት መዘጋት እና ከተለያዩ ሁኔታዎች አንጻር አራተኛው ዕትም የዘገየ ቢሆንም ቀጣዮቹንም ቅጾች በማከለ ለመዘጋጀት ስንሞክር የቆየንባቸው ግዜያት ፣ ከዚህ ባለፈ ተልዕኮአችንን መጽሔይትን ብዙዎች በቀላሉ ያገኙት ዘንድ በተለያዩ አማራጮች በድህረ ገጽ እና ጽሑፎቹን በንባብ እና በቅንብር በዩቲዩብ ላይ ለማቅረብ እየተዘጋጀን ነው። ስለሆነም መጸሔይቱ ሲጀመር እንደነበረው የግዜ ሰሌዳ በየ15 ቀኑ ዲጅታል በሆኑ መንገዶች በቴልግራም እና ሌሎች የማህበራዊ ትስስር ገጾች የሚለቀቅ ሲሆን የምታገኙባቸውን ቻናሎች እንደሚከተለው እገልጻለው።

Mission talk with Aman (https://t.me/NationsforGod)
Naoel's Perspective (https://t.me/NaolsP)
የቤሪያ ሰዎች በኢትዮጵያ (https://t.me/yeberiyasewoch)
መንፈሳዊ መጽሐፍት (https://t.me/amharicspritualbooks)

በተጨማሪም ጥያቄ እና አስተያየት ካልዎት
በስልክ ቁጥር :- +251920293652/ +251940094767 ይደውሉ
ኢ-ሜይል :- tsionamanuel9@gmail.com ያግኙን

አማኑኤል ገዛኸኝ

ማውጫ

- የመጽሐፍ ትርጉም ለምን አስፈለገ? 1
- ONE SOUL SAVED MATTER 3
- መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ 5
- የጽናት ተምሳሌቷ ሜርሊን ሎስዛሎ 6
- መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰሜን ኮሪያ እንዴት ገባ 10
- የጸሎት ጥሪ ለስልጤ የህዝብ ክፍል 12
- ዋይክሌፍ የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተቋም እና ስራዎቹ 13
- የክርስቲያኖች ስደት በሶማሊያ 15

የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለምን አስፈለገ?

የሎስ አንጀለሱ ተማሪ በኦሲዴንታል ኮሌጅ ሁለተኛ አመቱን ከጨረሰ በኋላ በወንጌል አገልግሎት ለመሳተፍ ወደ ጓቲማላ ተጓዘ። በአካባቢው ከሚገኙ ቤተክርስቲያኖች ጎን በመሆን ትራክቶችን በማሰራጨት እና ወንጌልን በመስበክ እያገለገለ ጎን ለጎን የስፓኒሽ ቋንቋ ክህሎቱን ለማሻሻል ጠንክሮ መስራት ጀመር። ወራት እያለፉ ሲሄዱ ግን አብዛኞቹ የጓቲማላ ሰዎች "ካክቺክል" የተባለ የራሳቸው ቋንቋ እንዳላቸው ተገነዘበ። ስለዚህ እርሱን ወደ ማጥናት ገባ፤ በመጨረሻም ቋንቋውን በመማር ከዛ በኋላ ላሉት 10 አመታት ከተርጓሚዎች ቡድን ጋር የካክቺክልን አዲስ ኪዳን መፅሀፍ በመተርጎም አብሮ ሰርቷል። ይህ ተማሪ የህይወቱን አሥር ዓመት ለትርጉም ለምን ሰጠ? ሰው መፅሀፍ ቅዱስን ለመተርጎም ህይወቱን ለምን ይሰጣል? ህይወትንም ለመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያደርጉ 4 ምክንያቶች ልነግርዎ እወዳለሁ እናም ብዙዎችን ለዘመናት ካንቀሳቀሰው ምክንያት ልጀምር እወዳለሁ።

1. <u>ፍላጎት</u>

መፅሀፍ ቅዱስን የተረጎመው የኦሲዴንታሉ ኮሌጅ ተማሪ በመጀመሪያ የጓደኞቹንና የቤተ ክርስቲያኖቻቸውን መንፈሳዊ ፍላጎት በቅርበት ተመለከተ። ወጣቱ ተማሪ እና ተርጓሚ ዊልያም ካሜሮን ታውንሴንድ ይባላል። በ1929 የካክቺክል አዲስ ኪዳንን ከጨረሰ በኋላ የዊክሊፍ የመፅሀፍ ተርጓሚዎችን ማቋቋም ጀመረ።

ታውንሴንድ ከሱ በፊት ከነበሩ ሚስዮናውያን በላይ መፅሀፍ ቅዱስ የሌላቸውን ቋንቋዎች ብዛት ማጥናት ፍላጎት አደረበት። እ.ኤ.አ በ 1933 “በአለም ላይ ቢያንስ አንድ ሺህ የሚሆኑ የተለያዩ ቋንቋ የሚናገሩ አንድም የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍል (በቋንቋቸው) የሌላቸው ጎሳዎች አግኝቻለሁ” ብሎ የጥናቱን ውጤት አቅርቧል።

ዛሬ፤ ለአስርት አመታት ምርምር እና ተልዕኮ ስራ ምስጋና ይግባውና 7,361 ቋንቋዎች እንዳሉ እናውቃለን። ከእነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ ሙሉ መፅሀፍ ቅዱስ ያላቸው 683 ቋንቋዎች ብቻ ናቸው። ያማለት ከ ዓለም ቋንቋዎች 9% የሚሆኑት ሙሉ የእግዚአብሄር ምክር አላቸው ማለት ነው። ተጨማሪ 1534 ቋንቋዎች አዲስ ኪዳን መፅሀፍ ቅዱስ አላቸው። ሆኖም 2163 ቋንቋዎችና ማህበረሰቦቻቸው የትርጉም ስራ እየተጠባበቁ ነው። በ1989 ወጣት ተማሪ እያለሁ ቻድን ስጎበኝ በዚያ አካባቢ ባየሁት ፍላጎት ተነቃቅቼ/ተገርሜ ነበር። በዚያ ፓስተር ቪክተር ከተባለ የኔጌድ ህዝብ በራሳቸው ቋንቋ መፅሀፍ ቅዱስ እንዲኖራቸው ለህዝቡ ትልቅ ልብ ያለው የቻድ ፓስተር ጋር ብዙ ቀን ማሳለፌን አስታውሳለሁ።የወሰድኩትን ስልጠና ይህንን ፍላጎት ለማሟላት እንድጠቀምበት ያበረታታኝ ነበር።

የዚያን ምሽት ስንነጋገር መቼም ካየሁት የበለጠ ብሩህ የሆነውን በከዋክብት ያሸበረቀ የአፍሪካን የምሽት ሰማይ እያደነኩ ነበር። ሰማያት የእግሂአብሄርን ክብር ያውጃሉ፣ ነገር ግን የኔጌድ በቻድ አካባቢ የሚገኙ ሌሎች ቋንቋዎች የሚናገሩት ሰዎች በቋንቋቸው መፅሀፍ ቅዱስ ሳይኖራቸው እንዴት የክርስቶስን ታላቅ ክብር ሊያዩ ይችላሉ?

ከፍተኛ የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉም ፍላጎት አለ። ይህ ፍላጎት ምንም ያህል ከፍተኛ ቢሆንም መፅሀፍ ቅዱስን ለመተርጎም ግን የመጨረሻው/ትንሹ ምክንያት ነው እላለሁ።ከፍላጎት በላይ በጣም ጠቃሚ የሆነ ሌላ ምክንያት አለ።

2. <u>የእግዚአብሔር ቃል</u>

በተለያዩ የአለም ቋንቋዎች ከፍተኛ የመፅሀፍ ቅዱስ ፍላጎት መኖር ለዘመናት(ከትውልድ ትውልድ) ተርጓሚዎችን ሲያነሳሳቸው ቆይቷል። ሆኖም (በራሱ) መፅሀፍ ቅዱስ መሆኑ እንጂ ፍላጎቱ ብቻውን አስገዳጅ አይሆንም። በሌላ አገላለፅ(አባባል) የመፅሀፍ ቅዱስ ተፈጥሮ በራሱ ለመተርጎም የበለጠ ጠንካራ ተነሳሽነትን የሚፈጥር ነው።

መፅሀፍ ቅዱስ ምንድን ነው? ከእግዚአብሄር የሆነ መገለጥ ነው። በ2ተኛ ጢሞቴዎስ 3፡16 ላይ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ፅፎአል”ቅዱሳን መፃሕፍት ሁሉ የእግዚአብሄር መንፈስ ያለባቸው ናቸው”... ጴጥሮስ ይህን ሀሳብ በ 2ተኛ ጴጥሮስ ሲያብራራው እንዲህ ይላል”ይህን በመጀመር እወቁ፤ በመፅሀፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፍቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሄር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ። የክርስቶስን ክብር ከማወቅና ከማሳወቅ የበለጠ ታላቅ ደስታ ምንድን ነው? በተጨማሪም፣ የእግዚአብሄር ቃል ለደህንነታችን ነው።ጳውሎስ በ2ተኛ ጢሞቴዎስ 3፡15 እንዲህ ሲል ፅፏል”ከህፃንነትህም ጀምረህ በክርስቶስ እየሱስ በማመን፣ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መፃህፍት አውቀሀል።”

የቀጠለ ....

በተጨማሪም ጳወሎሰ ቃሉ የእግዚአብሄር የመቀደሻ/የማንፃ መንገድ ነው ሲል ፅፎአል። በኤፌሶን የነበሩት ሽማግሌዎች ለስንብት ሲያገኛቸው "አሁንም ለእግዚአብሄር፤ ያንፃችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለፀጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ (ሐዋ 20፥32)።
በ1526 ዊልያም ቲንደል አዲስ ኪዳንን በኢንግሊዘኛ ተርጉሞ ሲያሳትም ይህን ጥረት ያደረገው ለመንፈሳዊ
እድገታቸው እንደሆነ ይናገራል። በመቅድሙም ላይ"በክርስቶስ የተወደዳችሁ/የምወዳችሁ ውድ ወንድሞችና እህቶች በመንፈሳዊ ህይወታችሁ እንድትታነፁ እና እንድትፀኑ አዲስ ኪዳንን ተርጉሜአለሁ" ብሎ ፅፎአል።
መፅሀፍ ቅዱስ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነና የድህነትም መምጫ መንገድ እንደሆነና አማኞችን
በእምነት ለመገንባት የመጣ እንደሆነ ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በሁሉም ቋንቋ የሚገኝ እንዲሆን የማይፈልግ ማን ነው?

4. ቤተ ክርስቲያን

መፅሀፍ ቅዱስን መተርጎም ለምን አስፈለገ?

ከቤተ ክርስቲያን ምንነት የተነሳ ከዚህ ከሁለቱ የበለጠ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሶስተኛ ምክኒያት አለ። ቤተ ክርስቲያንን በእግዚአብሄር እቅድ/አጀንዳ ውስጥ ልዩና ዘላለማዊ ስፍራ አላት። ከዚህም በላይ ያለ መፅሀፍ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ልትኖር አትችልም እንዲሁም ያለ ቤተ ክርስቲያን መፅሀፍ ቅዱስ ዓላማውን ማሳካት አይችልም። ቤተ ክርስቲያን ምንድን ናት? እግዚአብሄርን ለማምለክ በክርስቶስ ደም የተገዙ እውነተኛ አማኞች ስብስብ መሆኗ እርግጥ ነው። የአጥቢያ ቤተክርስቲን እግዚአብሄርን ለማምለክና እርስ በእርስ ለመበረታታት የሚገናኙ አማኞች ስብስብ ናት።
የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን በሐዋሪያት ስራ ውስጥ ስትመሰረት የእግዚአብሄር ቃል ለማስተማር የተሰጡ/የተጉ ነበሩ። ሉቃስ በሐዋሪያት ስራ 2፡42 ላይ እንደሚናገረው "በ ሐዋሪያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።" የቀደመችው ቤተ ክርስቲያን ስለ ምግብ ክፍፍል ቅሬታ ባጋጠማት ጊዜ ሐዋሪያት ምዕመናንን ሰብስበው የምግብ ክፍፍሉን በበላይነት የሚከታተሉ ሰባት ሰዎች እንዲመርጡ መመሪያ ሰጡ። ሐዋሪያት የስብከትና የማስተማር አገልግሎታቸው ለሌላ ስራ ጊዜ መስጠት እስከማይችሉ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አስተዋሉ። በሐዋሪያት ስራ 6፡4 ሐዋሪያት ለቤተክርስቲያን "እኛ ግን ለፀሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" ብለው ነገሯቸው። በተጨማሪም ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን አምልኮ ቃሉን ማእከላዊ ያደረገ እንዲሆን ለጢሞቴዎስ መመሪያ ሰጥቶታል። በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥13 ላይ "እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።" ብሎ ፅፎለታል። ሆኖም ጢሞቴዎስና ጉባኤው ቃሉን ማንበብ መስበክና ማስተማር ያዘወትሩ ነበር።

በተጨማሪም በማንበብ በመስበክ እና በማስተማር ቤተ ክርስቲያንን በእውነት ለማነፅ አማኞች በሚረዱት ቋንቋ ቅዱሳን መፃህፍትን ማግኘት ነበረባቸው። ጳውሎስ ማንም የማይረዳውን ቋንቋ መጠቀም ጥቅም አልባ መሆኑን ተረድቶ ነበር። በእርግጥ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፥1-26 ላይ ጳውሎስ በቆሮንቶስ የነበሩትን ክርስቲያኖች ትርጓሜ ሳይኖረው በልሳን የመናገር ልምዳቸውን ሲያርም ይታያል (ያርማል)። ማንም የማውቀውን ብዙ ከመናገር ይልቅ ለመረዳት የሚቻሉ አምስት ቃላትን መናገር እንደሚሻል በ 14፥19 ላይ "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።" ሲል ይገልፃል። በ 14፥26 "ሁሉ ለማነፅ ይሁን" ብሎ ዓላማውን አስረግጦ ይናገራል ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን የምትኖረው በቃሉ ውስጥ/በኩል እግዚአብሄርን ለማምለክ ነው። አማኞች የእግዚአብሄር ቃል ሊረዱት በሚችሉት ቋንቋ ሊኖራቸው ይገባል ይህም በእውነት አንዱ ሌለውን እንዲተናነጽ ይረዳል።

የእግዚአብሔር በግ

በአለም ዙርያ በሺዎች ለሚቆጠሩ ቋንቋዎችን መፅሀፍ ቅዱስ እጅጉን ያስፈልጋል። ሆኖም እንዳየነው መፅሃፍ ቅዱስን ለመተርጎም ይህ በጣም አሳማኝ ምክንያት አይደለም። መፅሀፍ ቅዱስን የምንተረጉመው የእግዚአብሄር ቃል ስለሆነ ነው ግን ይህም ለመተርጎም ከሁሉም የተሻለ ምክንያት አይደለም።
መፅሀፍ ቅዱስ ከምንነቱ በበለጠ ለማን ተፃፈው የሚለው የበለጠ ወሳኝ ነው። የተፃፈውም ለቤተክርስቲያን ነው። መፅሀፍ ቅዱስንም የምንተረጉመው ለቤተክርስቲያን ሲባል ነው።
ቃሉን መተርጎም የእግዚአብሄርን መንግስት እንዲስፋፋ ከምናደርግበት ታላላቅ ስራዎች አንዱ ክፍል ነው።ሆኖም ከነዚህ ሶስቱ ምክንያቶች የበለጠ አስፈላጊ የሆነ አንድ ተጨማሪ ምክንያት አለ፤ ምክንያቱም ሌሎቹ በፊቱ መቆም አይችሉም።

በዮሀንስ ራዕይ 4-5 ውስጥ ይህንን የመጨረሻውን ምክንያት በሐዋርያው ዮሀንስ የእግዚአብሄር ዙፋን ክፍል ራዕይ ውስጥ በግልፅ በዮሀንስ ራዕይ 4 ላይ ዮሀንስ በራዕይ ወደ ሰማይ ተወስዶ ነበር። እሱም በዙፋኑ ዙሪያ ያለውን አምልኮ፣ መላዕክት፣ ሽማግሌዎች እና ምስጢራዊ (ልዩ) ፍጥረታት እግዚአብሄር አብን ያለማቋረጥ ሲያወድሱት ይመለከታል። ወዲያውም ገና ይህንን በማየት ላይ ሳለ አንዱ መልአክ ሁሉንም አምልኮ ያስቆመ “መፅሀፉን ይዘረጋ ዘንድ ማህተሞቹን ይፈታ ዘንድ የሚገባው ማን ነው?" የሚል አዋጅ አሰማ።

ወደ ገጽ 4 ዞሯል...

"ONE SOUL SAVED MATTER" MOVEMENT "BLACK LIVES MATTER"

ይህ መላውን አለምን ያነቃነቀው የተቃውሞ ሰልፍ የቅርብ ትዝታችን ነው። እንደምናውቀው የሰብአዊ መብቶች መከበር ምሳሌ ተደርጋ በምትጠራው ሀያሏ ሀገረ አሜሪካ አንድ የሚኔሶታ ፖሊስ ጆርጅ ፍሎይድ የተባለን ጥቁር አሜሪካዊን በአሰቃቂ ሁኔታ ህይወቱ እንዲያልፍ ምክንያት ሆኖታል። የሟች የእርዳታ ጥሪንና የፖሊሱን ግድ የለሽነት የሚያሳይ ቪዲዮ በማህበራዊ ሚዲያዎች ወዲያው በመሰራጨቱ በፍጥነት የቁጣ ተቃውሞ ድምፆች መሰማት ጀመሩ። በተለይ በተንቀሳቃሽ ምስል ላይ የጆርጅ ፍሎይድን የሲቃ ድምፅ "I can't Breath!" (መተንፈስ አልቻልኩም) ለሰማና የመጨረሻውን ደቂቃዎች የተመለከተ ሰው ምን ያህል ልብን የሚሰብር እንደሆነ መረዳት አያዳግትም። የጆርጅ ፍሮይድ በአሰቃቂ መንገድ ህይወቱን ማለፉ ተከትሎ አሜሪካን አልፎ አውሮፓን ሲያነቃንቅ እንደ ነበር ይታወሳል። ይህ የሚያሳየው ማንም ሰው በህይወት የመኖር መብት እንዳለውና ማንም ይህን ውድ ህይወቱን ሊነጥቀው እንደማይችል የሚያሳይ ነው።

ሰው የክቡርነቱን ዋጋ ለመተመን ፈጣሪውን ማወቅ ያስፈልጋል። ከውድቀትም በፊት ይሁን በኋላ እግዚአብሄር በመልኩ ለፈጠረው ሰው የነበረው ዋጋ አልተለውጠም። የሰው ልጅ በውድቀት ውስጥም ቢሆን ፈጣሪው ይፈልገዋል፤ የሰው ልጅ በህይወት መኖር ለፈጣሪው ዋጋ አለው። "የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ፣ ደሙ በሰው እጅ ይፈሳል፣ በእግዚአበሄር አምሳል እግዚአብሄር ሰውን ሰርቶታልና።"{ዘፍ 9፡6} ይህን ስንመለከት ሰው በምደር ላይ መኖሩ ምን ያህል ውድና የከበረ መሆኑን እንረዳለን።

እግዚአብሄር በሀጢያት የወደቀውን የሰውን ዘር ዳግም ወደ ክብሩ ለመመለስ ያለውን ዘላለማዊ እቅዱን ደግሞ ስንመለከት ሰው ምን ያህል እጅግ የከበረና በህይወት የመኖሩ ዋጋው እጅግ ውድ መሆኑን ስንገነዘብ በአድናቆት መፍዘዛችን አይቀሬ ነው። ለዚህም ማሳያው ፈጣሪ ፍጡሩን እስከ መምሰል የደረሰበትን ሁኔታ መመልከት ከበቂ በላይ ነው። ተወዳጁ ዘማሪ ጆን ዶን "ሰው በአምላክ መልክ መፈጠሩ የሚያስደንቅ ነው፤ ነገር ግን አምላክ በሰው መልክ መገለጡ ደግሞ እጅግ የሚያስደንቅ ነው" በማለት እግዚአብሄር ለሰው ያሳየውን ፍቅር ገልጧል።

ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣበትን ሰውን የማዳን ተልዕኮ በማጠናቀቅ ለእኛ የሰጠን የራሱን ተልዕኮ ነው። ይህም "የሰው ልጅ የመጣ የጠፋውን ሊያድን" እንደ ሆነ ተናግሯል፤ በተግባርም አሳይቶናል።

በምሳሌም ያስተማረው ይህን ነው። ዘጠና ዘጠኙን በጎች አስቀምጦ አንዷን ፍለጋ መውጣቱ ከማንም በላይ ስለ አንዲቷ ነፍስ ግድ ይለዋል። በእነዚህ 2000 ዓመታት ውስጥ ብዙዎች ለተልዕኮው መሳካት ራሳቸውን አሳልፈው በመስጠት በሀጢያት ተጨማለቀው በሰይጣን አገዛዝ ተረግጠው በሞት መንደር የሚኖሩትን ለማዳን ከእግዚአብሄር ጋር ተሰልፈው በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩትን ህይወቶች አድነዋቸዋል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በራዕይ "ወደ መቄዶንያ ተሻግረህ ርዳን" {ሐዋ 16፡9} ለሚለው ጥሪ ፈጣን ምላሽ ሲሰጥ እንመለከታለን። ጆርጅ ፍሎይድ "መተንፈስ አቃተኝ ውሃ ጠማኝ እባክን አትግደለኝ!" በማለት ቢጣራም በጭካኔ ከተሞሉት ፖሊሶች በቀር ሊረዳው የሚችል ሰው በአጠገቡ አልነበረም።

ዛሬስ በሰይጣን አገዛዝ እየማቀቁ ለርዳታ የሚጣሩ ምን ያህል ይሆኑ? ሚልዮን ጊዜ ሚሊዮን ናቸው። ሰለክርስቶስ ለአንዴም እንኳ የመስማትን እድልን ሳያገኙ በየቀኑ በሀጢያታቸው ምክንያት እየሞቱ ላሉት ሰዎች የኛ ምላሽ ምን አይነት ነው? በ46 ዓመቱ ጆርጅ ፍሎይድ ህይወት ማለፍ እኛንም ጨምሮ መላውን አለም በቁጣ ከሞላውና የጥቁር መሞት ይብቃ፤ ፍትህ ለፍሎይድ በማለት በሺህ የሚቆጠሩ ለተቃውሞ አደባባይ ሲወጡ ተመልክተናል። "BLACK LIVES MATTER" የሚለው ዘመቻም ንቅናቄን ፈጥሯል።

ጥያቄዬና ሙግቴ ወንጌልን አንዴም ሳይሰሙ ወደ ሲኦል እየወረዱ ላሉት መቼ ይሆን ምንጮኸው? መቼስ ነው ድምፃችንን ከፍ አድርገን የማዳኑን ወንጌል የምናሰማቸው? "ONE SOUL SAVED MATTER" የሚል ለህዝቦች የመዳናቸውን ዜና የመናገር አለም ዓቀፋዊ ንቅናቄ ማየት የዘወትር ናፍቆቴና ረሀቤ ነው። ሰው በስጋ ከሚሞተው ሞት ይልቅ ክርስቶስን ባለማውቁ ምክንያት የሚሞተው ሞት የከፋ ነው። ሰዎች ክርስቶስን ባለማወቃቸው የሚደርስባቸውን ዘላለማዊ ሞት ከእነርሱ የበለጠ የምናውቀውና የምንረዳው እኛ የዳንን ነን። ጉዳዩ አንድ የእግር ኳስ ቡድን የመሸነፍና ያለመሸነፍ አይደለም፤ ጉዳዩ በህይወት የመኖርና ያለመኖር ትንቅንቅ ነው።

ሰው በህይወት የመኖር መብቱን ያገኘው ከእግዚአበሄር ነው። ይህን መብቱን ሰይጣን በሀጢያት በማታለል ሲወስድበት አላስችል ያላለው እግዚአብሄር ሰይጣንን በመቅጣት ለሰው በህይውት የመኖርን ዳግመኛ እድልን ሰጥቶታል። የመኖር መብታቸው ተገፍፈው ላሉት የአዳኛቸው ምላሽ እንዲህ ከሆነ የኛስ ምላሽ?

አቤኔዘር ጌታቸው
የተልዕኮ አስተማባሪ

ከገጽ 2 የቀጠለ....

ዮሀንስ ይህን ሰማና አምርሮ ማልቀስ ጀመረ ምክንያቱም ጥቅልሉን (መፅሀፉን) ሊወስድ የሚችል ስለሌለ። የእግዚአብሄር አላማዎች መፈፀም እንደማይችሉ አስቦ ይሆን? በዙፋኑ ዙርያ ከእንግዲህ ውዳሴ እንደማይኖር አስቦ ይሆን? ነገር ግን አንዱ ሽማግሌ ዮሀንስን በማልቀስ ፈንታ እንዲመለከት ነገረው ምክንያቱም የይሁዳ አንበሳ፣ የዳዊት ስር ድል ስላደረገ መፅሀፉን መውሰድ ይችላል።

ከዛም ዮሀንስ ወደ ዙፋኑ ተመለከተ፤ ግን ያየው አንበሳ አልነበረም። በግ እንጂ ለመስዋዕት የታረደ የሚመስል በግ። በጉም መፅሀፉን ከእግዚአብሄር አብ ወሰደ፤ ወዲያውም መንግስተ ሰማይ በውዳሴ ተጥለቀለቀ።

በዮሀንስ ራዕይ 5:9-10 ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች ከክርስቶስ ፊት ወድቀው ዘመሩ። “መፅሀፉን ትወስድ ዘንድ ማህተሞቹንም ትፈታ ዘንድ ይገባሃል፥ ታርደሀልና፥ በደምህም ለእግዚአብሄር ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከህዝብም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተህ ለአምላካችን መንግስትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሀቸው፥ በምድርም ላይ ይነግሳሉ።”

ከዛም ሁለተኛ መዝሙር አእላፋት ጊዜ አእላፋት ከሆኑ መላዕክት ወጣ፤ ”የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል ”

በጉመፅሀፉን ከፍቶ እንዲህ ያለ ውዳሴ ለመቀበል የተገባው ለምንድን ነው? ምክንያቱም ስለታረደ። እናም በመስቀል ላይ የመስዋትነት ሞቱ ለእግዚአብሄር ሀዝብን ገዛ፤ ለእግዚአብሄርም መንግስትና ካህናት እንዲሆኑ አደረጋቸው።

በዙፋኑ ዙርያ ባሉት ውዳሴዎች ውስጥ ክርስቶስ በ ማቴዎስ 28፡ 18-20 ላይ ለደቀመዛሙርቱ መፈፀም (መሟላት) እንሰማለን። እየሱስ ደቀመዛሙርቱን ሄደው አህዛብን ሁሉ እያጠመቁ ያዘዛቸውን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማሩ ደቀመዛሙርቱ እንዲያደርጓቸው አዘዛቸው። በተጨማሪም እስከ አለም መጨረሻ ድረስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቷል። በዮሀንስ ራዕይ 5:9 በዚያ ዘመን ማብቂያ ላይ በጉ ተወድሷል ምክንያቱም ለእግዚአብሄር” ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ከህዝብም ሁሉ” ሰዎችን ዋጅቶ ካህናት ስላደረጋቸው ነው። በሌላ አገላለፅ እርሱ የሚመሰገንበት ምክንያት ሙሽራው በሆነችው ቤተክርስቲያን በኩል ተልዕኮውን በመንፈስ ቅዱስ ሀይል ለአብ ክብር
ስለፈፀመ ነው።

ይህ ለቤተክርስቲያን እና ለእያንዳንዱ አማኝ ማጠቃለያ ነው። ሁሉም የሚያመራው ወደዚሁ ነው፤ በዙፋኑ ዙርያ የሚያመልኩ የተዋጁ ህዝቦች።

እናም እዚህ ጋር አሳማኝ ምክንያት እናገኛለን። የምንተረጉመው በጉ ስለተገባው ነው! ምስጋናችን ስለሚገባው ህይወታችን ስለሚገባው የእርሱን ልክ የሌለው ትልቅነት በተዋጁት ህዝቦቹ ቋንቋ እንዲታወቅ የማድረግ ጥረታችን ስለሚገባው ነው።

የእኛ ምላሽ

ያለውን ከፍተኛ ፍላጎት እና የተቀበልናቸውን ብዙ በረከቶች ግምት ውስጥ በማስገባት በአመስጋኝ ልብ በተቀበልነው ነገር ምን ልንስራ እንደተጠራን መጠየቅ የለብንምን? ከጥንቱ ሐዋርያ ከዮሀንስ ጋር ሆነን አይናችንን በዙፋኑ ዙርያ ባለው አምልኮ ላይ ማድረግ አለብን። የክርስቶስን ክብር ከማወቅና ከማሳወቅ የበለጠ ምን ደስታ አለ? እና ቃሉን መተርጎም የእርሱን መንግስት ከምናቋቁምበት እና ለእርሱ የዘላለም ውዳሴ ከምናመጣበት ታላላቅ ስራዎች አንዱ ክፍል ነው።

ዋና ጽሁፍ ፡ አሮን ሾቪክ
ትርጉም ፡ ህልዳና ብሩክ
የኮምፒውተር ጽሁፍ ፡ ሒወቴ ታደሰ

የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ

የክርስትናን ታሪክ በኢትዮጵያ ስንመለከት ወደ አንደኛው ክፍለ ዘመን ይወስደናል ይህ የረጅም ዘመን ታሪክ ደግሞ ሃገሪቷን ከሰሃራ በታች ካሉ ሃገራት ቀዳሚ የሚያደርጋት ነው። ቀዳሚ ከሚባሉት እና ለክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት ከሚነሱ መንገዶች የሐዋርያት ስራ መጽሐፍ 8፡ 26 – 38 ላይ ያለው የፊሊጶስ እና የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ታሪክ ነው።

ከዚህ ባለፈ በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት መንገድ በ330 ዓ.ም ከሶሪያ በመጡ ሁለት ወንድማማቾች ፍርምናጦስ (አባስላማ እና ዮዳስየስ) ሲሆን ኑጉስ ኢዛና ክርስትናን እንዲቀበልም ምክኒያት ሆነዋል። ብቻ በየትኛውም ይሁን በየትኛው ኢትዮጵያ ክርስትናን በመቀበል በዓለም ቀዳሚ ከሚባሉ ሃገራት ትሰለፋለች። በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከእስልምና መነሳት ጋር ተያይዞ አብዛኛው የአፍሪካ ሃገራት የእስልምናን መስፋፋት ተቋቁማ ክርስቲያን ሃገር ሆና መቀጠል ችላለች ይሁንና ከዚህ ጋርተያይዞ ከተቀሩት የክርስቲያን ሃገራት እርቀቷን ያሰፋ ነበር በዚህም የተለያዩ የታተሙ መንፈሳዊ መጽሐፍትና መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖባት ነበር።
በአሁኑ ግዜ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ክርስትና ባልሆኑ ሐይማኖቶች መስፋፋት ትልቅ ተግዳሮቶች እየገጠሟት ነው ይህም ቤተክርስቲያን እየሰራችው ያለውን የደቀመዝመር ማፍራት ስራ ጥያቄውስጥ የሚከት ሆኗል።
ከፍተኛ ቁጥር ያለው የክርስቲያን ማህበረሰብ ሆነ አዳዲስ ወደ ክርስትና የሚጨመሩ ሰዎች መጸሐፍ ቅዱስ የላቸውም ። በዙ ተቋማት እና አገልግሎቶች በዚህ መስክ በመሰማራት የመጸሐፍ ቅዱስ ትርጉም እና የማዳረስ ስራ ላይ እየተንቀሳቀሱ ያሉ ቢሆንም ገና ብዙ እንድንሄድ የሚጠይቀን የቤት ስራ መሆኑ ልብ ይሏል።

የኢትዮጵያው አባ ሩሚ(አባ አብርሐም)

መጸሐፍ ቅዱስ ወደ ግዕዝ የተተሮጎመው በ4ተኛው ክፍለ ዘመን በቅዱስ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ በ5ኛው ክፍለ ዘመን በ9ኙ ቅዱሳን ከግሪኩ ወይም ሰፕቶ አጀንት ከሚሉት ትርጉም ነው። ኢትዮጵያውያን አገልጋዮችም በዚህ ቅዱስ ስራም ተሳታፊዎች ነበሩ። አባ ሰላማ በነበሩበት ዘመን ተክለሃይማኖት እና ገብረ መስቀል የተሰኙ ሰዎች በዚህ የትርጉም ስራ ትልቅ ድርሻ እንደነበራቸው በገድለ አብርሃ እና አጽብሃ ላይ ተጸፎ እናገኛለን።

ከላይ በጠቀስናቸው አባቶች መጸሐፍ ቅዱስ በዚህ መልክ ከተተረጎ ነጎላ መጸሐፍ ቅዱስ እስከ 17 ክፍለ ዘመን በግዕዝ ቋንቋ እየተነበበ እና እየተተነተነ ቀጥሏል በ17ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ግዕዘኛው መጸሐፍ ቅዱስ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተተርጉሟል።

ከ1628 እስከ 1640 ዓ.ም ድረስ በጀርመናዊው ፒተር ሔሊንግ የተወሰኑ የመጸሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እና የተወጣጡ ጽሑፎችን ወደ አማርኛ ለመተርጎም ትልቅ ጥረት ተደርጎ ነበር ሆኖም ሙሉ በሙሉ በመተርጎም ለኢትዮጵያውያኖች ሁሉ ለማድረስ የተሳካላቸው አባ አብርሃም ናቸው።

አባ አብርሃም ማን ናቸው

ዶ/ር ጉስታቮ አሮን ቀደምት ወንጌላውያን በኢትዮጵያ በተሰኘ መጽሐፉ እንደጠቀሰው አባ አብርሃም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያገለግሉ የነበሩ ቄስ ናቸው። ትውልዳቸው በጎንደር እንደነበር በዘገባ መጽሐፉ እና በኢስንበርግ ባዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ተጠቅሷል።

አባ አብርሃም በአረብኛው አበሩሂም፣ አቡሪም አቢሩሚ የሚል አጠራር እና ስያሜ አለው። አባ አብርሃም መጸሐፍ ቅዱስን እንዴት ወደ አማርኛ ተረጎሙት? አባ አብርሃም የ28 ዓ.ም ወጣት እያሉ ወደ ቅድስት ሃገር እየሩሳሌም በግብጽ በኩል መንፈሳዊ ጉዞ አድርገው ነበር። እየሩሳሌም ካዩ በኋላም ወደ ሲሪያ፣ አርሜኒያ እና ፐርሺያ አቅንተዋል ወደ ሃገራቸው ኢትዮጵያም ከመመለሳቸው በፊት ወደ ህንድ ተጉዘዋል። አባ አበርሃም በሃምሳ አመታቸውም ላይ ወደ ግብጽ ለሁለተኛ ግዜ ተጓዙ በዚያም የነበሩ ገዳሞችን እና አብያተክርስቲያናትን ጎበኙ። በካይሮ በነበረበት ጊዜ በጠና ታምሞ ነበር ። ሆኖም የቅርብ ጓደኛቸው በነበረው ፈረንሳዊው አስሊን እርዳታ ሞትን ማምለጥ ችሏል ።

ዶ / ር ጉስታፍ አባ አብርሃም አረብኛ ፣ ፐርሺያኛ ፣ ጣሊያን ፣ ግሪክ እና ሌሎች ቋንቋዎችን እንደሚያውቅ እና እርሱ የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ምሁር መሆኑን ጽፈዋል ። በግብጽ የፈረንሳይ ኤምባሲ ምክትል አማካሪ በነበሩት አስሊን የትምህርት እድል ያገኙ ሲሆን አማካሪውም አባ አብርሃምን መጸሐፍ ቅዱስን ወደ ኢትዮጵያ የስራ ቋንቋ እንዲተረጉሙ ጠይቀዋቸው ነበር ። አባ አብርሃምም የአስሊን ምክር በድስታ ተቀብለው የትርጉሙን ስራ ቀጠሉበት። ምክትል አማካሪው አስሊም አባ አብርሃምን የተለያዩ ግብዓቶችን በማቅረብ ይደግፉአቸው ነበር።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል...

የጽናት
ተምሳሌቷ ሜርሊን ሎስዛሎ

ታሪካችን ታሪክ በማይረሳቸው የወንጌል ጀግኖች የተሞላ ነው። የክርስትናን ህይወት ጎዳና በመጓዝ ሂደት ብንገዳገድ፣ ፈተናው ቢበዛ፣ መከራ ቢጋረጥብን የዕብራውያን ጸሀፊ እንደነገረን እንደደመና የከበቡን ምስክሮች አሉልንና ፊታችን ከተደቀኑት ተግዳሮቶች አልፈን የዕምነታችንን ጀማሪ እና ፈጻሚ ክርስቶስን ተመልክተን እሩጫውን በዕምነት እንድንሮጥ ተመክረናል። በታሪክ ብዙ ሺ ሚሲዬናውያን የክርስቶስን ወንጌል ይዘው ወዳልደረሳቸው ህዝቦች ሄደዋል፣ መስዕዋት ዘር ሆነዋል።



እኔ ከሚያስደንቁኝ ታሪኮች ውስጥ አንዱ ፓፓዋ ኒውጊኒ ሀውና የተባሉ ህዝቦችን በወንጌል ለመድረስ የሄደች የሜርሊን ሎስዛሎ የተባለች ሚሲዬናዊት/ መጸሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ታሪክ አንዱ ነው ። ይህች የወንጌል አርበኛ ሚሲዬባዊነት በእርሷ ውስጥ ከ 5 ዓመቷ ጀምሮ ያደገ ጥሪ ነው፤ ይህንም ጥሪ ለመፈጸም የቋንቋ ጥናት እና ካልቸራል አንትፖሎጂ ትምህርቶችን ተከታትላ የዋይክሌፍ የመጽሐፍ ተርጓሚዎችን ተቀላቀለች። ሲኪ ወንዝ አቅራቢያ የሚገኙ ሀውና የሚባሉ ህዝቦችን ለመድረስ ከባልደረባዋ ጋር ወደ መንደሩ ሲደርሱ ነዋሪዎች ሁሉ ወጥተው ተቀበሏቸው። የመጀመሪያ ጥያቄያቸውም ምን ልታደርጉ መጣችሁ ነበር? ሜርለንም እኛ ከእናንተ ጋር ለመኖር መጣን በማለት መለሰች ይህ እንግዴ የ24 ዓመት መጽሐፍ ቅዱስን በዚህ ህዝብ ቋንቋ ተርጉሞ ክርስቶስን ለዚህ ህዝብ ለመስጠት የተጀመረው ጉዞ ምዕራፍ አንድ ነበር። ይህ ህዝብ የሚነገር ቋንቋ እንጂ የተቀረጸ ፊደላትም ስላልነበሩት መተርጎምም ቀላል አይሆንም። በነጋታው ሜርለን ከባልደረባዋ ጋር በመሆን የትርጉም ስራ ለመጀመር ቋንቋቸውን ለመማር ይጀምራሉ አስተርጓሚ የለም፣ የሚረዳ የለም ትርጉም ሚፈልጉት ነገር ላይ ለሰዎቹ ቢገባቸው በማለት መጠቆም፣ መደብደብ የመጀመሪያው ነበር፤ ሜርለን ስትናገር ወደ ቤቶቻቸው ጠጋ አልንና በእጃችንን እየደበደብን ሃውስ ሃውስ እያልን መጮህ ጀመር ሁሉም በመገረም ያዩን ነበር ከመሃላቸው አንድ ሰው "ኡማጋ" ብሎ ተጣራ ቤት ለሚለው ቃል የነሱ ትርጉም ነበር በደብተራችን ላይ በስነ ቃል አጻጻፍ መሰረት አሰፈርነው ይህ እንግዴ እግዜብሐር በዘፍጥረት መጽሐፍ ህዝቦችን በቋንቋ፣በነገድ እና በወገን ከበተነት ግዜ አንስቶ የተጻፈ የዚህ ህዝብ የመጀመሪያው ቃል ነበር። የቋንቋውን ፊደላት፣ አናባቢ እና ተነባቢዎችን ለመለየት አምስት ዓመት አካባቢ የፈጀ ሂደት አላፏል።

በዚህ ሒደት ለተልዕኮ አብራት የማጣች ባላደረባዋ መቀጠል ስላልቻለች አቋርጣ ሄደች ሜርለንም ብቻዋን ይህን ትልቅ የቤት ስራ መስራት ቀጠለች ሄደቱ አድካሚ፣ ተስፋ አስቆራጭ እና በብዙ ፈተናዎች የተሞላ ነበር። ከዚህ ጎን ለጎን ትምህርት ቤት ከፍተው ቋንቋውን ማስተማር፣ የጤና አጠባበቅ ላይ መስራት ጀምረው ነበር በዚህም በትርጉም ስራዋ ላይ አብረዋት የሚሆኑ የሃገሬው ሰዎችን ማብቃት እና ማሳተፍ ቻለች፣ ከዚህ ባለፈ እሷ ወደ ማህበረሱ ስትመጣ የነበረው በአማካይ የመኖር የዕድሜ ስሌት 32 እና 33 ነበር ይህ በቆይታዋ እግዚአብሔር በአስደናቂ መልኩ ቀይሮታል በአማካይ የመኞር እድሜ ወደ 52 እና 53 ከፍ ያለበት ነበር። ሜርለን ትርጉም ስራው ግማሽ ላይ በደረስንበት ዓመታት ደከምኩ ትላለች ጎጆ ቤቴ ውስጥ ሄኞ አንድ ምሽት ማልቀስ ጀመርኩ ጌታ ሁይ ከበደኝ አልኩት እግዚአብሔርም ሜርለን እነዚህ ህዝቦች የፈጠርኳቸው እኔ ነኝ፣ ከአንቺም በላይ እወዳቸዋለው፣ ቋንቋውንም ከማንም በላይ የማውቀው እኔነኝ አለኝ በረታሁ መብራቴን አጥፍቼም ተኛሁ።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል...

ከገጽ 5 የቀጠለ....

በምክትል አማካሪው ድጋፍ በታላቅ ጥንቃቄ እና ትጋት አባ አብርሃም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍን ተርጉሞ ለመጨረስ አስር አመት ፈጀባቸው። አባ አብርሃም ለትርጉም የሚያስቸግሩ እና በግዕዝ ቃላት ፊደላት ውስጥ የሌሉትን ምክትል አማካሪው አስሊን ከስርቱን፣ ሴፕቱአጀንት ትርጉሞች እና ከተለያዩ መዝገበ ቃላት በማጣቀስ ይደግፏቸው ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም አባ አብርሃም የተለያዩ ቋንቋዎችን ማንበብ ይችሉ ነበርና ይህ ደግሞ የትርጉም ስራው ውጤታማ ይሆን ዘንድ ረድቶአቸዋል። ይህን ታላቅ ስራ ከጨረሱ በኋላ አባ አብርሃም በእየሩሳሌም ለመቀበር ፍላጎታቸውን ተናገሩ ይህንንም መጋቢት 2,1811 በስዊዝ ቄስ ክርስቶፈር ቡካርድት የተጻፈው ደብዳቤ ላይ ተገልጾአል። ወንጌላዊ ክርስቶፈር እንደገለጹት አባ አብርሃም ወደ እየሩሳሌም እንደደረሱ የተላላፊ በሽታ ተጠቂ ሆኑ በዚህም በዚያው አመት መጋቢት ወር መግቢያ ላይ ህይወታቸው እንዳለፈ ተዘግቧል።

አባ አብርሀም በሞተ ጊዜ የተረጎመው የመጽሐፍ ቅዱስ የእጅ ጽሑፍ በእስሊን እጅ የተጠበቀ ነበር ። በታህሳስ 1804 (እ.ኤ.አ.) የሜዲትራኒያ አካባቢ የቤተክርስቲያን ተልእኮ ኃላፊ የነበረው ዊልያም ዮኔት ወደ ግብፅ በመሄድ ከአስሊን ጋር ተገናኝቶ የአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ተጠናቀቀ ። አሊን ከጄቲ ጋር በተገናኘች ጊዜ በአባ አብርሃም የተተረጎመውን ውድ የመጽሐፍ ቅዱስ የእጅ ጽሑፍ ክፍል ወስዶ እራሱን አስተዋወቀ ። ጽሑፉ በ 9539 ገጾች በአስተርጓሚው አባ አብርሀም የእጅ ጽሑፍ ተጽፎ ነበር ። የተፃፈው በኢትዮጵያ የግዕዝ ፊደላት ሲሆን እጅግ የተዋበ ፣ ልዩ እና ቀጥ ያለ አጻጻፍ ነበር (qum tsehuf}) የቤተክርስቲያኗ የሚስዮን ማህበር እና የእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ ለአባ አብርሃም የእጅ ጽሑፎች ሙሉውን ክፍያ ሳይሆን ተገቢውን ክፍያ ጠይቀዋል ። የጠየቁት ዋጋ 1200 ዶላር ብቻ ነበር (አንድ ሺህ ሁለት መቶ ፓውንድ) ነበር ይህ በዛሬ የምንዛሬ ዋጋ ከ 36,000.00 (ሰላሳ ስድስት ሺህ) የኢትዮጵያ ብር ጋር ተመጣጣኝ ነው። የእንግሊካን የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር በተጠየቀው ክፍያ ተስማማ። በዚያም ወዲያውኑ በታላቋ ብሪታንያ ባለሙያዎች ፣በቋንቋ ምሁራን አራቱ ወንጌላት በ 1816 ዓ.ም ፣ ሙሉው አዲስ ኪዳን በ 1821 ዓ.ም እና ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በ 1832 ዓ.ም ተመረመረ ።

አባ አብርሀም ብዙዎች ወደ ሚናገሩት አማርኛ ቋንቋ መጸሐፍ ቅዱስን በመተርጎም ለኢትዮጵያውያን ታላቅ በረከትን አምጥተዋል። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን በሚረዱት ቋንቋ እንዲያነቡ እና የመዳንን ምስጢር ማወቅ እንዲችሉ አድርጓል። ስለሆነም የኢትዮጵያ ክርስቲያን ህዝብ የአባ አብርሃም ከፍተኛ ባለዕዳ ነው ። ስሙ በተረጎመው መጽሐፍ መግቢያ ክፍል ላይ ህያው ይሆናል ። (ሀኪዳን አባ አብርሃም 1929)

የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

ወንጌላዊው አናሲሞስ ነሲቡ (አባ ገመቺስ) ከወለጋ የተገኘ መጸሐፍ ቅዱስን ወደ ኦሮሚኛ የተረጎመ እንቁ ሰው ነው። የትርጉም ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ የስዊድን ሰዎች አማካሪዎች አብረውት ነበሩ። አስቴር ገነኖ የግል ረዳቱ ነበረች። የኦሮሚኛ አዲስ ኪዳን የታተመው እ.ኤ.አ. በ1886 ዓ.ም ነው ሙሉውም የኦሮሚኛ መጽሐፍ የታተመው በ 1891ዓ.ም ነው። የአናሲሞስ ነሲቡ የጉልበት ፍሬ የሆነው የኦሮሚኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከአባ አብርሃም ትርጉም እና ከስዊድን መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ጋር የሚነጻፀር ነው።

የትግርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

የትግርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ከ 1861 እስከ 1952 ዓ. ም በተከበሩት አባት አለቃ ተወልደ መድህን ገቡሩ የተተረጎመ ነው። አለቃ ተወልደ መድህን ገብሩ በማሚሻም ትግራይ ውስጥ የተወለዱነት ስፍራ ነው። በትርጉም ሥራው የስዊድናዊው ዊንክቪስት አማካሪው እንደነበር ይታወቃል ። የአዲስ ኪዳን የትግርኛ ትርጉም በ 1901 ዓ.ም ታተመ አጠቃላይ የትግሪኛ መጽሐፍ ቅዱሱ ደግሞ በ1948 መታተም ችሏል ።

አለቃ ተወልደ መድህን ትግርኛ ፣ ትግራዋይ ፣ ግዕዝ ፣ አማርኛ ፣ አረብኛ ፣ ይብራይስጥ ፣ ጣልያንኛ እና ስዊድንኛ ቋንቋን እንደሚያውቁ ዶክተር ጉስታቭ አሮን ያረጋግጣሉ ። መጽሃፍ ቅዱስ ከዚያ ወዲህ በሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በየተወሰነ ጊዜ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ታትመዋል ። በ1ኛው ክፍለ ዘመን በግዕዝ እና በ 2ኛው ክፍለዘመን ደግሞ በአማርኛ ፣ በኦሮምኛ ፣ በትግርኛ እንዲሁም በሌሎች ብሄራዊ ቋንቋዎች ኢትዮጵያ መጽሃፍ ቅዱስ በማግኘት ተባርካለች ። እስከ መጨረሻው ቀንም ይህ በረከት ወደ ሌሎች ቋንቋዎች የሚቀጥል ይሆናል።

አዲሱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም

በ1923 ዓ.ም እ.ኤ.አ. በንጉሰ ነገስት ኃይለሥላሴ ትእዛዝ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ከግዕዝ ወደ አማርኛ በኢትዮጵያውያን ሙሁራን እንዲተረጎም ተደረገ የህትመቱም ስራ በለንደን ተካሄደ። መጽሐፉ የታተመው በአራት ክፍሎች ነበር ይህም የሆነው በግዕዝ እና አማርኛ ጎን ለጎን የተጻፈ ስለነበር ነው። በተጨማሪም በየካቲት 27, 1939ዓ.ም በንጉሰ ነገስት ኃይለሥላሴ ትእዛዝ መሠረት ሰባት ኢትዮጵያውያንና ሶስት የውጭ ምሁራንን ያቀፈ ኮንፈረንስ ተዘጋጀ በዚህም የተሻሻለውን ትርጉምም በ 1944 እ.ኤ.አ. አቅርቧል ይህም በአባ አብርሃም የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ ከይብራይስጥና ከሲሪሚ ጋር በማነፃፀር ነው።
ይህ የሆነበት ምክንያት የአብ አብርሃም ትርጉም ለአማርኛ ሰዋስው ትኩረት ከመስጠት ይልቅ የቃል በቃል ትርጉም ስለነበር ነው። ይህ ትርጉም በ 1953 A.D በብርሃን እና ሰላም ማተሚያቤት የታተመ ነበር ።



.... የቀጠለ

ይህ ትርጉም እ.ኤ.አ. ከ 1923 ዓ.ም የግዕዝ ትርጉም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተቀበለችውን ወይም የተስማማችበትን የብሉይ ኪዳን ክፍል የያዘ ነበር። ይህ የተሻሻለ ትርጉም እ.ኤ.አ. በ 1980 ዓ.ም የአዲስ ኪዳን እርማት ከተደረገ በኋላ የታተመ ነበር ።

እነዚህ አራቱ የተከበሩ ፣ የተባረኩ አባቶች እና እናት አባ አብርሃም ፣ አናሲሞስ ነሲቡ ፣ አስተር ገኖ እና አለቃ ተዎልደ መድህን የኢትዮጵያ ክርስትና መሪ ሃይሎች ናቸው ብለን ብንናገር ማጋነን ሚሆንብን አይመስለኝም ። በእውነቱ በእኔ አስተያየት እነሱ የሚቀጥለው ትውልድ እንደ ታሪካዊ ሰዎች መታየት ስለሚያስፈልጋቸው የመታሰቢያ ሐውልት ይገባቸዋል ። እነዚህ አባቶች እና እናት ምንም እንኳን በቁሳዊ ፣ በገንዘብ እና በመሠረታዊ ፍላጎቶች ድጋፍ ቢኖራቸውም እንኳ ማየት የሚችሉት ብርሃን ማየት እንደምንችል ያረጋገጡን እነሱ ነበሩ። እነሱ ስለሰጠን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። “እነዚህን ሰዎች ያሳደገችው ቤተክርስቲያን የተባረከች ፣ አባቶች እንዲሁም እነሱን እና ዘራቸው የተባረኩ ናቸው።

የተወደዳችሁ ጓደኞቼ ፣ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በአገራችን አምስት ቋንቋዎች እያቀረበ ይገኛል ። እንዲሁም በ25 ቋንቋዎች ውስጥ የአዲስ ኪዳን መጻሐፍት አለ ። አሁንም 30 ቋንቋዎች ይቀራሉ። ብዙ መከር አለ እናም በዚህ የመከር ሥራ መካፈል አስፈላጊ ነው። በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሰዎች በአስተማሪዎች የተሰጡትን ስብከቶች ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ እያስገቡ ስለሆነ ከምንግዜውም በላይ መጽሐፍ ቅዱስን እያነበቡ ነው፤ እናም መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ በጣም እንደሚያስፈልግ እና የአቅራቦት እጥረት እንዳለበት ግን ግልፅ ነው። የሕትመት መሣሪያው ወደ አገራችን እንዲገባ እግዚአብሔርን መጠየቅ ያለብን ጊዜ ይህ ነው ለእግዚአብሔር የማይቻል ነገር የለም። አሜን!!

አማኑኤል ገዛኸኝ
የተልዕኮ አስተማባሪ
ጭማሪ ጽሑፍ (ዋይክሌፍ ኢትዮጵያ ፣ ባይብል ፎር ኢትዮጵያ 2014)

ከገጽ 6 የቀጠለ....

የጽናት
ተምሳሌቷ ሜርሊን ሎስዛሎ





24 ዓመታት ወሰደብን ግን መጸሀፍ ቅዱስን በሃውና ህዝቦች ቋንቋ ተረጎምነው እየሱስንም ሰጠናቸው። የመጸሀፍ ቅዱሱንም ሽፋን አረንጓደ እንዲሆን መረጡ የጫካው ቀለም እንዲይዝ ። እነዚህ መጸሐፍ ቅዱሶች ታትመው ሚመጡበት ቀን ትልቅ ክብረበዓል አደረጉ ከሌላ ጎሳዎች ሰዎችን ጋበዙ፣ ቤቶቻቸውን አስውበው አሳምረው ይጠብቁ ነበር ሁሉም ሰው ወንዙ ዳር ቅዱሱን መጽሐፍ ይዘው ሚመጡ ጀልባዎች እስኪደርሱ በጉጉት ይጠብቅ ጀመር ጀልባዎቹ እየታዩ ሲመጡ ከፍተኛ ፌሽታ፣ ደስታ፣ ዝላይ እና ጩኸት ሆነ የአባታችን መጸሐፍ በቋንቋችን እያሉ ጮኹ። ወስደውም መጽሐፍ ቅደዱስን ከፍተው በእጃቸው እያሹ የአባታችን መፀሐፍ በቋንቋችን ይሉ ነበር ።

ሜርለን ወደዚህ ህዝብ እስከሄደችበት 1967ዓ.ም ድረስ ይህ ህዝብ በወንጌል ያልተደረሰ ነበር ስለዚህ ጌታም ለመስማት እንደሞተላቸው ስለነሱም ሞት ድል እንዳደረገ በእርሱ በማመን የዘላለም ህይወት እንደሚገኝ ለመስማት 1967 ዓመታትን ጠብቀዋል ሜርለን ሎስዛሌ የተባለች የወንጌል አርበኛ የህይወቷን (ወጣት ሆና ሄዳ ጎልማሳ ሆናእንደወጣች) በኩሩን ስለአንድ ህዝብ ለመስጠት የወሰነች ሴት ባትኖር ማንያውቃል ዛሬም ድረስ ወንጌል ያልደረሳቸው ከምንላቸው ውስጥ ይጠቀሱ ነበር። ዛሬ በዓለማች ካሉ 17,424 የህዝብ ክፍሎች መካከል 7,424 ህዝቦች፣ በምድራችን ኢትዬጰያ 32 የህዝብ ክፍሎች ይህን የምስራች ወንጌል ለመስማት የዘመናችን ሜርሊን ሎስዛሎን እየጠበቁ ነው፤ የድሜያቸውን በኩር፣ ጉብዝናቸውን ብቃት እና አቅማቸውን ስለወንጌሉ ሚሰዉ። 7,424 ህዝቦች አምላክ ከሞተላቸው፣ ከተነሳላቸው በእርሱ በማመንም ያለውን የዘላለም ህይወት ለመስማት 2020 ዓመታትን ጠብቀዋል እየጠበቁ ም ነው ዛሬ ታዲያ ዘማሪዋ እንዳለች ማነው የዘመኔ አርበኛ፣ የዘመኔ ወንጌል ሰባኪ በሰልፍ መሃል የሚበረታ የነዚህ ህዝቦች የመጠበቂያ ዘመን ያብቃ የሚል የወንጌሉ የምስራች ወደ ህዝቦች ሁሉ ይደርስ ዘንድ እኔነት በሌለበት ህይወት የሚወጣ የምስራቹን ይዞ የሚሰማራ ።

አንተ የተኛ ንቃ ለወጌል አርበኝነት እንድትበቃ፣ ግፈፍ አይንህ ላይ ያደረከውን ጭንብል ፣ አፍርስ ልብህ ላይ የገነባኸውን ክልል ለመሻገር ያሰረህን። ጌታው ያመጣል በሰጠህ መክሊት ስንት አተረፍክበት ይልሃል ቀበርኩት ያልክ እንደሆን እመነኛ አንተ ሃኬተኛ ባሪያ ትባላለህ ከሽልማቱም ትጎድላለህ እመነኝ ከሽልማት መጉደል ብቻ ሳይሆን በሃኬተኝነትህ የተነሳ ትቀጣለህ ከተዘጋጀው ክይወት፣ ከሰማዩም ኑሮ ትሰረዛለህ።

ሜርሊን ሎስዛሎ እና ሌሎች የእምነት አባቶች ሩጫውን ቀድመውን ሮጠዋል ስለዚህ ወንጌል ብዙ ነገራቸውን አጥተው ብዙ ሽልማትም ተቀብለዋል ታሪካቸው ብል በማይበላው መዝገብ ላይ በደማቅ ሰፍሯል በመጨረሻውም ቀን የሀውና ህዝቦች በበጉና በዙፋኑ ፊት ለምስጋ ሲቀርቡ ሜርሊን ሎስዛሉ አብራ ትደምቃለች አክሎቿ ናቸውና ታንጸባርቃለች። ይህ የዚች የወንጌል ጀግና ታሪክ ነው የአንተ፣ የአንቺ፣ የእኔ፣ የእናንተ እና የእኛ ታሪክ ግን ምንድነው ፤ በህይወታችን ምን እየሰራን ፣ ምንስ ልንሰራበት አቅደናል አንድ ነገር ግን አውቃለሁ እኛ ለእግዚአብሔር የተቀደስን ምርጥ ዕቃዎች ነን ከዚህ ጌታ ጋር በተልዕኮው ሜዳ አብረነው እንድንሰለፍ ጩኸቴ ነው ።

የማንቂያ ደውሉ ተሰምቷል እና እናስተጋባው!!

አማኑኤል ገዛኸኝ
የተልዕኮ አስተማባሪ

ስለእግዚአብሔር ቃል ህይወትን አደጋ ላይ መጣል: መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰሜን ኮሪያ እንዴት ገባ

ኪም ዳ-ቢን በፍርሃት ስሜት ዙሪያውን ተመለከተች ። እኩለ ሌሊት በኋላ ነው ጨረቃም በቤቷ አቅራቢያ ባለው ጫካ ውስጥ ተደብቃ ስትራመድ ብርሃኗን በሷ አቅጣጫ ታበራለች። በዙሪያዋ ማንም የለም አየሩም ቀዝቃዛ ነበር።
በጃኬቷ ስር አንድ ትንሽ አካፋ ይዛለች።የተቀመጠላትን ምልክት መሬት ላይ አገኘች እናም የቻለችውን ያህል በፀጥታ መቆፈር ጀመረች። ከትንሽ ቁፋሮም በኃላ የምትፈልገውን አገኘች ። ከላስቲኩ ከረጢት ላይ አፈሩን አራገፈችና በውስጡ ያለውን ለማውጣት ሽፋኑን ማንሳት ጀመረች። ትንሹ መጽሐፍ ከላስቲኩ አፈትልኮ ወደቀ ነገርግን ድምጹ ያን ያህል ሚሰማ አልነበረም ቢሆንም ግን ድምፁ በሌሊት ፀጥ ሲል ፣ እንደ ጥይት ተኩስ ይሰማል። ዙሪያዋን ትመለከተች - ማንም አላስተዋላትም ። እናም መጽሐፉን በጃኬቷ ኪስ ውስጥ አድርጋ ተደብቃ ወደ ቤቷ ተመልሳ ሄደች። ቤቷ ከገባች በኋላ መጋረጃዎቹን ዘጋች መጽሐፉን ከኪሷ አውጥታ ከፍታ ማንበብ ጀመረች ።

"በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድ እንኳ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም። በበትርህ እና በትርህ ያጽናኑኛል"።

ጽሑፉን በቆየ የኮሪያኛ ቃላት የተጻፉ ነበሩና ቃላቱን ለመረዳት በጣም ተቸግራ ነበር ፤ ነገር ግን ይህ ትንሽ መጽሐፍ ለሷ በጣም ውድ የሆነው ንብረቷ ነው ። ማንበቧን ከጨረሰች በኋላ እንደገና በጸጥታ ወደ ውጭ ወጣች ትንሹን መጽሐፍ ቅዱስ ከቦርሳዋ ውስጥ አውጥታ እንደገና ወደ ጉድጓዱ ውስጥ አስገባች አፈሩንም ሸፈነችው። በተቻለችው መጠን ድምጽ ሳታሰማ ምንም ዓይነት ዱካ አለመተዋን አረጋገጠች ። ወደ ቤቷ ተመልሳ ወደ መኝታዋ ሄደች ይህ በማንም ሰው ያደረገችውን ያላየበት ሌላ ምሽት እና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያሳለፈችበት ሌሊት ሆነ ይህ ብቻ ሳይሆን ግን መጽሐፍ ቅዱስን መያዝ የሚያስገድልባት ሰሜን ኮሪያ ሌላ ሌሊት ነው።

በሰሜን ኮርያ ያሉ ህጻናት ልክ አሜሪካውያን ህጻናት ለገና ስጦታ ተደብቆ የእለቱ ቀን ሲሰጣቸው እንደሚደሰቱ እና ሚይዙትን ሚጨብጡትን እንደሚያጡት መጸሐፍ ቅዱስ ሲያዩ እንደዚያ ነው የሚያደርጋቸው። ኪም ሳንግ ሃዋ ስትናገር በእኛ ቤት አንድ የተደበቀ የልብስ ማስቀመጫ ነበር በአስራ ሁለት አመቴ ድንገት አገኘሁት ለምን እንደሆነ ባላውቅም እጄን አሾልኬ መዳበስ ጀመርኩ መጸሐፍ እንዳለ ሲሰማኝም በቀዳዳው አሾልኬ አወጣሁት። ከፍቼም ማንበብ ጀመርኩ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይ እና ምድርን ፈጠረ ይላል።ድንገት ሰውነቷ ተንቀጠቀጠ መጸሐፉንም ጣለችው።

ኪም ሳንግ ስትናገር በጣም ፈርቼ ነበር። ይህ መጽሐፍ በሃገራችን ህገ ወጥ እንደሆነ አውቃለሁ ይህ ያገኘውት መጽሐፍ ህይወቴን ሊያሳጣኝ የሚችል ነው። መጽሐፍ ቅዱሱን ማንሳት ፈርቼ ነበር ግን እዛ መሬት ላይ ደግሞ መተው አልችልምአይኔንም ጨፍኜ አንሳሁት ወደ ሳጥኑም ከተትኩት ።

ከዛም ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርኩ። ለአስተማሪዬ ልንገራት ? ወይስ ወደ ፖሊሶች ሄጄ ላመልክት ? ለሚቀጥሉት 15ቀን ሌላ ነገር ማሰብ አልቻልኩም ነበር። ይህን ህገወጥ መጽሐፍ ማጋለጥ እንደነበረብኝ አውቃለሁ ግን ደግሞ ማጋልጠው ቤተሰቤን ስለነበር አልቻልኩም እና ደግሞ ብዙ ጥያቄዎችም ነበሩኝ ይህ አምላክ ማን ነው ? ምንድን ነው? የሚሉ ።

ሰሜን ኮርያ መጽሐፍ ቅዱስ ሊመስል ይችላል ብላችሁ ከምትጠብቁት ፈጽሞ የተለየ ነው። አሁን ላይ ሰዎች መጠቀም ባቆሟቸው የቀድሞ የኮርያ ቋንቋዎች የተጻፉ እና በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው።
ኦፕን ዶር የተባለው ተቋም በቅርቡ ከሰሜን ኮርያ በድብ የወጡ መጽሐፍ ቅዱሶችን እና መንፈሳዊ ጽሐፎች ደርሰውር ነበር ይህ የሆነበት ምክኒያት ደግሞ ሰሚን ኮርያ ያሉ አማኖች አዳዲስ መጸሐፍ ቅዱሶችን እና ጽሐፎችን ህይወታቸውን ለአደጋ አጋልጠው በሚሰሩ የመፀሐፍ ቅዱስ በድብቅ በሚያስገቡ ሰዎች ምክኒያት ነው።
እነዚህ ከሰሜን ኮርያ የወጡት የመጸሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ መንፈሳዊ መጽሐፎች እና የመዝሙር ደብተሮች አስደናቂ ናቸው። አብዛኛዎቹ 1920ዎቹ ጀምሮ እስከ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ግዜ ድረስ የነበሩ እና በ19ኛው ክፍለዘመን እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ በነበሩ የአጻጻፍ ስልቶች የተጻፉ ናቸው። እነዚህ ጽሑፎች እና አጻጻፋቸው አሁን ላይ የሚጠቀማቸው የለም መጸሐፍ ቅዱስ እና መንፈሳዊ ጽሑፎች ግን ለእነዚህ አማኞች ውድ የሆኑ እንደልብ ማያገኟቸ ናቸውና ደቀው ከትውልልድ ትውል ያስተላልፏቸዋል።

አንዳንድ አማኞችም ድንበር አልፈው ወደ ቻይና የመግባት እድል ሲኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስን በኦድዮ እንዲያገኙ ይደረጋል። ይህ ግን ግዜያዊ መፍትሄ ነው ሰዎች ከሰሜን ኮርያ ወደ ቻይና ሚሄዱት የተለያዩ መገልገያዎችን ለመግዛት ብቻ ነው ቶ ሎ መመለስ አለባቸው ምክኒያቱም የቤተሰባቹ አባል ሃገር ከድቶ ሸሸ ተብሎ ማንም ቤተሰቡ እንዲታሰር እና እንዲጉላላ ስለማይፈልግ ። አንዳንድ ግዜየአማኞች መጠለያ ይሄዳሉ እዛም ወደ ሃገራቸው ይዘው ሚመለሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ድምጽ ቅጂ ያገኛሉ።

.... የቀጠለ

የኦፕን ዶር አገልጋይ ከአንድ ሰሜን ኮርያዊ የትንሽ እና ድብቅ የክርስቲያኖችን ህብረትከሚመራ ወንድም ጋር የነበረውን ቆይታ እንዲህ ይገልጸዋል፡፡ ያለፈው አመት ይህ ወንድም የመጽሐፍ ቅዱስ የድምጽ ቅጂ እበና ሌሎች መንፈሳዊ መጽሐፎች ይደርሰዋል እናም አስራ አምስት ሰዎች ላሉበት እሱ የሚመራው ህብረት ላይ በስፋት ይጠቀምበታል፡፡

ሰሜን ኮርያ መንግስት የተለያዩ የስርጭት ማቋረጥ ሙከራ ያደርግበታል እንጂ አንድ የራዲዮ ፕሮግራም አለ በዚያም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እንዲተላለፍ ይሞከራል ይህ በቻ ሳይሆን ይህን የራዲዮ ፕሮግራም ሲሰማ የተገኘ ሰው በጣም ከባድና አሰቃቂ ቅጣት እንዲደርስበት ይሆናል ሆኖም ግን ከ30,000 በላይ ሰሜን ኮሪያውያን ይህን የራዲዮ ፕሮግራም ያዳምጣሉ፡፡ እነዚህ የራዲዮ ፕሮግራሞች ለአማኞቹ በጽሐፍ ቅዱስን በንባብ ያሰማሉ ይህ ብቻ ሳይሆን የትንታኔ ስራንም ይሰራሉ፡፡ እንደ መጽሀፍ ቅዱስ ትምህርተቤትም የሚያገለግሉ ፕሮግራሞች አሏቸው በዚህም የሶስት አመት የሴሚናሪ ትምህርት መለኪያ ያለው ስልጠና ይሰጣል፡፡

ምንም ያህል ህይወትን የሞት አፋፍ ላይ የሚጥል ውሳኔ ቢሆንም ሰሜን ኮሪያውያን ለመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ረሃብ በጣም ጥልቅ ነው መጽሐፍ ቅዱስን ለማግኘት ሆነ ለመስማት የማይከፍሉት ዋጋ ግን የላቸውም፡፡

በመቅበር ፣ በራዲዮ በማስተላለፍ ፣ በድብቅ ወደ ሃገር በማስገባት ደብቆ ለትውልድ በማስተላለፍ ይሁን በሳጥን ውስጥ በመቆለፍ በሰሜን ኮርያ ግን የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነው፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በኩል በሰሜን ኮርያ ያሉ አማኞች እምነት በማጠናከር፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር በማስታወስ እና ለእነርሱ የሆነውን እውነት እያስታወቃቸው ነው፡፡

ወደ ሰሜን ኮርያ በድብቅ በሚገቡት መጸሐፍ ቅዱሶች እና ደቀመዝመር ማድረጊያ መርጃ መሳሪያዎች እግዚአብሔር በዚያ ያለችን ቤተክርስቲያን እያበረታ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ስለ እርሱ በጽናት የሚቆሙ አማኞችን እያፈራ ይገኛል፡፡

በብዙ ስለእነዚህ አማኞች እንጸልይ ዘንድ በጌታ ፍቅር እጠይቃለው፡፡ አንዳንድ ግዜ ነጻነት ባለበት ቦታ ስንኖር ወንጌል የሚያሰከፍለው ዋጋ ምንድን ነው የነሚለውን ብዙዎች አናውቅም፤ ይህን ለማወቅ እንደነሱ የአንባገነን አገዛዝ ሰለባ መሆን አለብን ብዬ አላምንም፡፡

በእጃች ያለው ቅዱስ ቃሉ በነጻነት ማግኘታችን ደግሞም ማንበባችን ትልቅ እድል እንደሆነ ማስተዋል ይኖርብናል፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያለሰንን ቁኝት መጨመር እና ማብዛት ልንዘነጋው የማይገባ ተግባር መሆን አለበት ፡፡

በሰሜን ኮርያ የሰብአዊ መብታቸው ተከብሮ አማኖች በነጻነት ጌታን ማምለክ ይችሉ ዘንድ እንጸልይ፡፡ በእነዚህ ቦታ ያሉ አማኞች በምን ያህል ሰቆቃ እንደሚያመልኩ አስቡት፣ የእግዚአብሔር እጅ በሰሜን ኮርያ እንዲገለጠ መጸለይ ይኖርብናል፡፡

በክርስቶፈር ሰመርስ የተጻፈ
ትርጉም ፡ አማኑኤል ገዛኸኝ

የጸሎት ጥሪ ለስልጤ ህዝብ ክፍል

የሕዝቡ ቁጥር- 1,535,000
ዋና ቋንቋ- ስልጤ
የሕዝቡ ዋነኛ ሃይማኖት - እስልምና (96.00%)
ክርስትና ተከታዮች ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 2.00%
የወንጌል አማኞች ከ ህዝቡ በ % ሲሰላ - 0.09%

መግቢያ / ታሪክ

የጉራጌ የህዝብ ክፍል ብዙውን ጊዜ ሦስት የተለያዩ ንዑስ ቡድኖችን እንዳቀፈ ይነሳል እነሱም የሰሜን ፣ የምስራቅ እና ምዕራባዊያን ናቸው። በምስራቃዊ ንዑስ ቡድን ውስጥ ትልቁ ቡድን የሆኑት ስልጤ እራሳቸውን እንደ ጉራጌ አድርገው አልቆጠሩም ፣ እንደውም በ2000 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) በ (የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል) ውስጥ የሲልጤ ዞን የራሳቸውን የአስተዳደር ክፍል ለመመስረት በአንድነት ድምጽ ሰጥተዋል። “ስልጤ” የሚለው ቃል የዘመናዊ ሰልጤ ቋንቋ ተናጋሪ ሰዎች ቋንቋ ነው። የዛሬዋ ሰልጤ ከዋና ዋና የታሪካዊ ንዑስ ክፍሎች የተወጣጣች ናት እነርሱም -አዝርኔት ፣ በርበር ፣ አልቺቾ ፣ ዊሪሮ ፣ ሜልጋ (ወይም ኡልባረግ) እና ስልጤ (ወይም ሱሙስልጤ) ናቸው። ስልጤ የሚለው ስም (ንዑስ ቡድኑ) የተገኘው ጄን ስልጤ ከሚባለው የቀደምት ዘር ቅድመ አያት ስም ነው ። ዘመናዊው ስልጤ የሚለው ስም ይህን ቅድመ አያት መታሰቢያ ለማረግ እናም ስልጤዎች ከሐዲያ ሰዎች የድሮ እስላማዊው የሱልጣን ንጉሠ ነገሥት ጋር ታሪካዊ ዝምድና እንዳላቸው መታሰቢያ እንደመሆናቸው ለማሳየት እንደመረጡት ይናገራሉ። እስከ ሃያኛው ክፍለ-ዘመን አጋማሽ ድረስ ስልጤዎች የጉራጌ አካል እንደሆኑ ይቆጠር ነበር (ነገርግን በሰባት ቤት ጉራጌ አድያ ወይም ሃድያ በሚል ስም ይጠራሉ)። ሌሎች ስያሜዎች እስላም ወይም የምስራቅ ጉራጌ (ከቋንቋቸው በኋላ የምስራቅ አካባቢ ጉራጌ ቋንቋን የሚመሰርተው አካል ሆነ) ። እ.ኤ.አ. በ1991 የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ ዛሬ እራሳቸውን የቻለ የብሔር ማንነት ለማቋቋም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ጀመሩ ። ስልጤዎች የስልጤን ዞን ከጉራጌ ዞን አስተዳደር ነፃ በማድረግ ረገድ ከአስር ዓመት በኃላ ስኬታማ መሆን ቻሉ።

የሚገኙት የት ነው ?

የስልጤ ሕዝቦች በደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ጎሳዊ ቡድኖች ናቸው ። የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ላይ የዛሬውን የስልጤ ዞን ላይ ሰፍረው ይገኛሉ ። ቁጥራቸው በርካታ የሆነ ስልጤዎች በአዲስ አበባ ፣ አዳማ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ አነስተኛ ከተሞች እና ሌሎች ከተሞች ውስጥ ነጋዴዎች ወይም አነስተኛ የገበያ ሱቆች ነጋዴዎች ሆነው ይኖራሉ ። በገጠራማ አካባቢዎች የሚገኙት ስልጤዎች የእንሰት እርሻ እና በአርሶ አደርነትን የሚኞሩ ናቸው።

እምነታቸው ምንድን ነው?

አብዛኛው የስልጤ ህዝብ ሙስሊም ነው።

ፍላጎቶቻቸው ምንድን ናቸው?

ድህነትን ፣ ሰብአዊ ልማት ፣ የገጠር ልማት ፣ የምግብ ዋስትና ፣ የአቅም ግንባታ ፣ የግብርና እና የንግድ ልውውጥ ፣ የግል ሴክተር ልማት ማጎልበት እና የኢንዱስትሪ ልማት ችግሮችን መፍታት ሁሉ አስፈላጊ ናቸው ። የክርስቶስን ፍቅር ለስልጤ ሰዎች ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚዎች አሉ በተለይም በጤና እና በትምህርት መስክ ። ብዙ ቤተክርስቲያን ልትጠቀማቸው የምትችለው የአካባቢ ሀብትና የውስጥ መሪ መሆን ለሚችሉት የአገሬው ተወላጅ ሰዎች በድንኳን ሰራሽ አገልግሎት እራሱን/ሷን ለመደገፍ እንዲችሉ የአንድ ጊዜ ድጋፍ መስጠት ትችላለች ። ወጣቶች አብዛኛውን ጊዜ በአንድነት ስለሚሰበሰቡ ከስልጤ ወጣቶች ጋር አብሮ ለመስራት ብዙ እድሎች አሉ። ለእነሱ ብቸኛው መዝናኛ መሰብሰብ እና መጫወት ነው። እንደ እግር ኳስ ወዳጆች ፣ የውሃ ድጋፍ እና የመሳሰሉት ሚኒስትሮች ሊረዱን ይችላሉ ። የአካባቢውን ሠው በቋሚነትና በነፃነት ለመርዳት እድሎች አሉ።

የጸሎት ርዕስ

1. የእግዚአብሔር በረከት ለስልጤ ህዝብ እንዲበዛ እንጸልይ
2. በዚያ ያሉ አማኞች እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ
3. ሚሲዮናውያን ወደ ስልጤ ህዝብ እንዲንቀሳቀሱ
4. በዚያ ያሉ ጥቂት ሚሲዮናውያን እግዚአብሔር እንዲያበረታቸው፣ በሚያስፈልጋቸው አቅራቢያት እንዲባርካቸው እንጸልይ ።

ምንጭ :- ጆሹዋ ፕሮጀክት
ትርጉም:- ኪሩቤል ጎበና
አርትኦት :- አማኑኤል ወንድማገኝ

የዋይክሌፍ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ታሪክ

በ1917 ዊሊያም ካሜሮን ታንሰንድ የተባለ ሚሲዮናዊ በስፓኒሽ ቋነቋ የተፃፈ መፅሐፍ ቅዱሶችን ለመሸጥ ጓቲማላ አቀና። ግን ብዙ ሰዎች መፅሐፍቱን መረዳት ባለመቻላቸው ተደነቀ። እነርሱ በሚናገሩት ካክቺክል በተባለው ቋንቋ የተተረጎመ መፅሐፍ ቅዱስ አልነበረም። ካሜሮን ሁሉም ሰው መፅሐፍ ቅዱስን መረዳት አለበት ብሎ ስለሚያምን ‹‹ ዘ ሰመር ኢንስቲቲዩት ኦፍ ሊንጉዊስቲክስ›› ወይም አሁን ‹‹ SIC›› በመባል የሚታወቀውና ሠዎችን መፅሐፍ ቅዱስን በመተርጎም የሚያሰለጥን የቋንቋ ትምህርት ቤት ገባ። ስራው እያደገ ቀጥሎ እ.ኤ.አ በ1942 ካም የዊክሊፍ የመፅሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎችን በይፋ አቋቋመ።

በሚቀጥሉት አስርት አመታት ዊክሊፍ ብዙ ትልልቅ ክስተቶችን አክብሮአል። እነዚህም እ.ኤ.አ በ1951 ከተጠናቀቀው የመጀመሪያው የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም እስከ እ.ኤ.አ በ2000 የተተረጎመው 500ኛው ትርጉም ያሉ ናቸው። በዚያው ጊዜ ደግሞ ዊክሊፍ በ2025 እስካሁን መፅሐፍ ቅዱስ በሌለው እያንዳንዱ ቋንቋ የትጉም ፕሮጀክቶችን ተጀምሮ ለማይት እቅድ አውጥቷል።

ራዕይ 2025

በ1999 መሪዎቻችን እየሰራን በነበረበት ፍጥነት ከሄድን የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ለሚያስፈልገው እያንዳንዱ ቋንቋ ትርጉም ከመጀመሩ በፊት ቢያንስ እ.ኤ.አ 2150 እንደሚሆን ተገነዘቡ። በአለም ዙሪያ በየቀኑ የወንጌሉን መልካም ዜና ሳይቀበሉ የሚጠፉትን ሰዎች ሲያስቡ ይህን ተልዕኮ ለማሳካት አዲስ ግብ እንዲቀዳጁ እግዚአብሄር እየጠራቸው እንደሆነ ተሰማቸው። በ2025 መሪዎችን እስከ አሁን አንድም የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም በቋንቋቸው ለሌላቸው አዲስ ትርጉም ፕሮግራም ተጀምሮ ለማየት ምንም ነገር ለማድረግ ዝግጁ ናቸው።

.... የቀጠለ

ዛሬ ቢያንስ 2000 ቋንቋዎች አሁንም የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል፤ ዊክሊፍ እነዚያን ቋንቋች በተቻለ ፍጥነት ለመድረስ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በፍጥነት እየሰራ ይገኛል። ዊክሊፍ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም እንዲጠናቀቅ በዓለም ዙሪያ ካሉ ብዙ ድርጅቶች ጋር በጋራ ይሰራል። በዛሬው ጊዜ ቢያንስ 2000 ቋንቋዎች አሁንም የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል ነገር ግን ብዙዎቹ የሚገኙት ለመድረስ አስቸጋሪ በሆኑባቸው አካባቢዎች ነው። በተለያዩ የአለም ክፍሎች ውስጥ የመተርጎም ጥረቶች ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ትንሽ እይታ እነሆ

አፍሪካ

በቆዳ ስፋት እና በህዝብ ብዛት ከአለም ሁለተኛ እንደ መሆኗ አፍሪካ በአለም ላይ ካሉት አጠቃላይ ቋንቋዎች ሰላሳ በመቶዎች የሚገኙባት አህጉር ናት። ቢያንስ 700 የሚሆኑትም በአፍሪካ ያሉ የቋንቋ ቡድኖች ትርጉም ያስፈልጋቸዋል። ምንም እንኳን አፍሪካ በዓለም ውስጥ ታላቅ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም ከሚያስፈልጋቸው ቦታዎች ብትመደብም አጥቢያ ቤተክርስቲያኖች በፍጥነት እያደጉና በአገራቸው ካለው የወንጌል ስርጭት እና ደቀ-መዝሙር ብዜት ራዕይ ጋር እየቀላቀሉ ነው።

አሜሪካዎች

11 የተለያዩ የሰዓት ቀጠናዎችን በሚሸፍኑት አሜሪካዎች ውስጥ ወደ 1000 ያህል የዓለም ቋንቋዎች ይገኛሉ። የመፅሀፍ ቅዱስ ትረጉም ፍላጎቱ በዓለም ላይ ካሉት በዝቅተኛ ደረጃ ሲገኝ ቢያንስ 400 የቋንቋ ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል። ነገር ግን ከ120 የሚበልጡ ቋንቋዎች አሁንም የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም እንዲጀመር በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

ኤሲያ

በእግዚአብሄር የተስፋ እና የፍቅር መልዕክት ዓለምን ለመድረስ በእስያ የሚገኙ ግለሰቦች እና የሚሲዮን ድርጅቶች አብረው እየሰሩ ይገኛሉ። በብዙ የእስያ ሀገራት ውስጥ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ሚስዮናዊያን ከዓመታት በፊት ጀምረውት የነበረውን ስራ አሁን አካባቢው ውስጥ በሚገኙት እየተከናወነ ይገኛል። እስያ በዓለም ዙሪያ የወንጌል ስራ በማስፋፋት ረገድ ዋና አጋር ወደመሆን በፍጥነት እየመጣች ነው። ከ 850 የሚበልጡ በእስያ የሚገኙ ቋንቋዎች አሁንም የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም እንደሚያስፈልጋቸው ይታመናል።

አውሮጳ

ጳውሎስ መጀመሪያ የወንጌሉን መልካም ዜና ወደ አህጉሪቱ ካደረሰባት እ.ኤ.አ ከ 50ዓ.ም ገደማ ጀምሮ መፅሀፍ ቅዱስ በተለያዩ ቋንቋዎች በመላው አውሮጳ ተተርጉሟል። በአሁኑ ጊዜ ለብዙ የአውሮጳ የምልክት ቋንቋዎችና ለብዙ ዘመናት ወደ አውሮፓ ለተሰደዱ በርካት ተፈናቃዮች የትረጉም ስራ እየተካሄደ ይገኛል። እነዚህ ማህበረሰቦች በቀጥታ ለልቦቻቸው በሚናገሩ ቋንቋዎች ወንጌልን መስማት አለባቸው እና ለእነዚህ ሰዎች የመፅሀፍ ቅዱስ መተርጎም በእግዚአብር ፍቅር እንዲደረሱ ቁልፍ ሚና አለው።

ፓስፊክ

የፓስፊክ ክልል በሺዎች የሚቆጠሩ ደሴቶችን ትልቁ ውቅያኖስ ውስጥ ያጠቃልላሉ። ከአውስትሪሊያ በረሀ ጀምሮ ጥቅጥቅ እስካለው ሞቃታማው የፓፓዎ ኒው ጊኒ ደን ድረስ እና የቫኑአቱ የዘንባባ ተክሎች ድረስ ፓስፊክ የ1300 ቋንቋዎች መገኛ ነው (ይህም የዓለም 20 በመቶ አይሞላም) የፓስፊክ ደሴቶች በአለም ላይ ትልቅ የመፅሀፍ ቅዱስ ትርጉም የሚያስፈልግባቸው ቦታዎችን ይወክላል። ይኸውም በፓፓዎ ኒዉ ጊኒ ብቻ ቢያንስ 400 ቋንቋዎች የመፅሀፍ ቅዱስ ትጉርም አልተሰራላቸውም።

ስለ ዋይክሌፍ መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ተቋም እና ስራቸው ይበልጥ ለማወቅ
እና ስራቸውን ለመከተል ቀጥሎ ያለውን ድህረ ገጽ እንዲጎነኙ ጋበዝን www.wycliffe.org

ትርጉም ፡ ህልዳና ብሩክ
የኮምፒውተር ጽሁፍ ፡ ረድኤት ብርሃኑ

ሶማሊያ
ዓመፅ ፣ የእርስ በእርስ ጦርነት እና ከፍተኛ ስደት

ሶማሊያ በእርስ በእርስ ጦርነት ፣ በጎሳ እና በዓመፅ፣ በእስላማዊ አክራሪ የእስልምና ጦር ቡድኖች አረንቋ ውስጥ ትገኛለች ። ወደ ክርስትና መለወጥ የሶማሊያን ቤተሰብ እና የጎሳዎችን እንደ መካድ ተደርጎ ይወሰዳል ። ሶማሌዎች ወደ ክርስትና ተለውጠዋል ተብለው ከተጠረጠሩ በቤተሰብ አባላት እና የጎሳ መሪዎች ጥቃት ይደርስባቸዋል ፣ ያስፈራሯቸዋል አልፎ ተርፎም ይገድሏቸዋል። ቀድሞ የእስልምና እምነት ተከታዮች የነበሩ ክርስቲያኖች በአልሸባብ ታጣቂዎች ከፍተኛ ኢላማዎች ተደርገው ይወሰዳሉ እናም ወደ ክርስትና መቀየራቸው ሲታወቅ በተገበኙበት ቦታ ላይ ብዙውን ጊዜ ይገደላሉ ።

አሸባሪው የእስላማዊ ቡድን አልሸባብ የሶማሊያ የሕይወትን ገጽታዎች በሙሉ ለመቆጣጠር መሠረት እንዲሆን የሸሪአ ሕግ እንዲሰርፅ ይፈልጋል ። ይህ ቡድን ክርስቲያኖችን ከአገሪቱ የማስወጣት ፍላጎት እንዳለው ደጋግሞ ገልጾአል። የውጭ ጂሀዲስቶችም በአገሪቱ ውስጥ ይገኛሉ የእስልምና ጭቆና ግን በታጣቂዎች ብቻ የሚፈጸም አይደለም ። ክርስቲያኖችም በቤተሰብ አባሎች፣ በዘመዶቻቸው እና በአጠቃላይ ከኅብረተሰቡ ከባድ ስደት ይደርስባቸዋል ።

ወደ ክርስትና እንደተለወቱ ታወቀ ማለት በሁሉም ቦታ በግል ፣ በቤተሰብ ፣ በማህበረሰብ እና በሀገር ውስጥ በሁሉም የሕይወት መስኮች ለሕይወት አስጊ የሆነ አደጋ ውስጥ ይገባሉ። ይህ የስደት አካሄድ ለየት ያለ እና ሶማሊያን በከፍተኛ የክርስቲያኖች ስደት ምድብ ውስጥ ከፍ እንድትል ያደረጋት ነው።

በዚህ ምክንያት አብዛኛዎቹ የሶማሊያ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ሙሉ በሙሉ ምስጢራዊ ያደርጋሉ ። ነገር ግን አደጋዎች ቢኖሩም ሶማሌዎች በኢየሱስ ወደ ማመን እየመጡ ናቸው - አንዳንዶቹ በተአምራዊ መንገዶችም ጭምር።

<u>የስደት ምሳሌዎች</u>

ባለፉት ዓመታት ሁኔታው እየተባበሰ መጥቷል ። እስላማዊ ታጣቂዎ ቡድኖች ክርስቲያን የሆኑ እና አመራራቸውን የማይቀበሉትን ማደናቸውን አጥብቀው ቀጥለዋል። በ2017 ነሐሴ ወር በሀርጌሳ ሶማሌላንድ ተዘግቶ የነበረንቤተክርስቲያን መልሶ ለመክፈት በመንግስት የተደረገው ጥረት በአካባቢው ላይ መስሊም ማህበረሰብ በተነሳ ተቃውሞ እና አመጽ ሳይከፈት ቀርቷል።
የ2020 የአለም ዋች ዝርዝር በሚለቀቅበት ወቅት ክርስትና ለእስላማዊ ታጣቂ ቡድኖች ጥቃቶች በጣም የተጋለጠ እንደሆነ አመልክቷል።
ለደህንነት ጉዳዮች ሲባል በአሁኑ ጊዜ ምንም ምሳሌዎችን ሊታተሙ አይችሉም።

..... የቀጠለ

ሶማሊያ
ዓመፅ ፣ የእርስ በእርስ ጦርነት
እና ከፍተኛ ስደት

ለሶማሊያ ህዝብ እና ሀገር ጸልዩ

• የሶማሌ ህዝብ ከ 99 በመቶ በላይ ሙስሊም ሲሆን ህብረተሰቡም ሙስሊም እንደሆነ ይታወቃል ። እስልምና የመንግስት ሐይማኖት ነው። በነዚህ ጦርነቶች እና ስደቶችም መካከል ጌታ ቤተክርስቲያኑን መገንባቱን እንዲቀጥል ጸልዩ።

• በአፍሪካ ቀንድ ያሉ የሶማሌ ሕዝቦች በተለያየ ሁኔታ ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ጸልዩ ። ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ጥልቅ ረሃብ እና ጥማት እንዲኖራቸው ይፀልዩ ።

• ኦፓን ዶር የ ኤስ ኤ እንደገመተው በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ክርስቲያኖች ቁጥር በመቶዎች ብቻ የሚቆጠሩ እንደሆነ ይገምታል ። አማኞች ወንጌልን ለማካፈል ደፋሮች ይሆኑ ዘንድ ጸልዩ ።

• በሶማሊያ አማኞች መካከል የበረቱ እና መንፈሳዊ አርአያ የሚሆኑ አማኞች እንዲገኙ ጸልዩ ። ባሉ በተለያዩ ህብረቶች መካከል አንድነት እንዲጨምር ጸልዩ ።

Ø የክርስቲያኖች ቁጥር ስታትስቲክስ የኦፓን ዶር የኤስ ኤ ግምት ነው::

ምንም እንኳን ኦፕር ዶር እንደተባለው ተቋም ግምት የክርስቲያኖች ሞት ባይዘገብም በዓለም ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የክርስትያኖች ግድያ እና እና የአብያተ ክርስቲያናት ጥቃት የደረሱት ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሃገራት ውስጥ ናቸው ። በናይጄሪያ ፣ ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ (ሲአር) ፣ ደቡብ ሱዳን ፣ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ እና ቡርኪና ፋሶ ብቻ 2,476 ክርስቲያኖች በእምነታቸው ሰማዕት እንደሆኑ ሪፖርት ተደርጓል። በናይጄሪያ 1,350 እና በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ 924 ሪፖርት ተደርጓል። በናይጄሪያ ክርስትያኖች በፉላኒ ታጣቂ ሃይሎች ኢላማ የተደረጉ ናቸው በቦኮሀራም ፣ በ ISWAP እና በክርስቲያኖች ማህበረሰቦች እና በአብያተ ክርስቲያናት ላይ ጥቃት በሚሰነዝር በመግደል ፣ በማሰር እና በአስገድዶ መድፈር የሚካሄዱት በበርካታ የታጠቁ የወንጀል ቡድኖች ነው ።

ቡርኪናፋሶ ለመጀመሪያ ጊዜ በ28ኛ ደረጃ ላይ የዓለም የስደት ደረጃ 50 ዝርዝር ውስጥ ገብቷል ። የአልቃይዳ እና እስላማዊ መንግስት (ISIS) በሃገሪቱ ውስጥ በብዛት በመገኘታቸው በክርስቲያኖችም ሆነ በመንግስት ላይ ጥቃት ለመሰንዘር አስችሏቸዋል። እ.ኤ.አ. በ 2019 በቡርኪና ፋሶ ቤተክርስትያን በጽንፈኞች እምነታቸውን እንዲክዱ ወይም እንዲሞቱ ለሚጠይቋቸው አክራሪዎች እምቢ በማለታቸው በተደጋጋሚ በአምልኮ አገልግሎት ወቅት እና በኋላ ጥቃት ሲሰነዘር እንደነበር ይታወቃል። ይህም የስደትን አስከፊ ገጽታ እና በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔርን ህዝቦች ሃያል እምነት የሚያሳይ ነው።

ያለጸሎት መንፈሳዊ አለም ላይ ምንም ልናደርግ አንችልም። ወንጌል ደግሞ ትልቅ ተጋድሎ የሚፈልግ ነው ምክኒያቱም መጸሐፍ ቅዱስ የዚህ አለም ገዢ አይምሮቸውን እነዳሳወረ ይናገራልና። ስለዚህም ሰዎች ካሉበት ጨለማ ይወጡ ዘንድ አይናቸው ተከፍቶ ማየት ይችሉ ዘንድ በጸሎት ቅጥር ልንቆም ይገባል።

ስደት የዘመናት የቤተክርስቲያን እና አማኞች የኑሮ መልክ ነውና አዲስ አይደለም በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን እግዚአብሔር ሃይሉን እንዲገልጥ፣ ለአማኞች መበርታት እነደዲቸሉ አጥበቀነን እንጸልይ መልዕክቴ ነው ተባረኩ ።

ምንጭ :- ኦፕሬሽን ዎርልድ
ኦፓን ዶር ዩኦስ ኤ
የማህበረሰብ ጥናት፡ በጆንሰን ቲ እና ዙርሎ ጊ ከወርልድ ዳታቤዝ

ትርጉም :- አማኑኤል ገዛኸኝ